January 4, 2012

ለአቶ ማሪዮ ጉዊዶ ፊሪጌሪ
የማልታ የስደተኛ ኮሚሽነር
የአገር ውስጥ ጉዳይና ፍትሕ ሚኒስቴር
ማልታ

ክቡር ሆይ፤

ይህንን ደብዳቤ የምንጽፍልዎ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) ተብሎ ከሚጠራው ድርጅታችን ሲሆን ጉዳዩም **በአገርዎ በማልታ ከአንድ ዓመት በላይ ታስረው የሚገኙትን ኢትዮጵያውያንን በተመለከተ** ነው፡፡ የጋራ ንቅናቄያችን ከእነዚህ ኢትዮጵያውያን ጋር በየጊዜው የሚገናኝ በመሆኑ ለረጅም ጊዜ ከመታሰራቸው ባሻገር ያሉበት የእስር ሁኔታ እጅግ አስከፊ መሆኑን ጠንቅቆ ያውቃል፤ መረጃም አለው፡፡ **ከእነዚህ ስደተኞች ውስጥ በሕክምና እጦት የሚሰቃዩ ሴቶች፣ በሚጥል በሽታ፣ በስነልቦና ቀውስ፣ በአእምሮ ጤና መቃወስ የተቸገሩ አካለ ስንኩላንና ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ብላቴናዎች ከእስረኞቹ የጥቂቶቹ ሁኔታ ነው፡፡**

እነዚህ ኢትዮጵያውያን ለጥገኝነት ያቀረቡትን ጥያቄ እንዲመለከቱላቸውና ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን ወሳኝ የሆኑ ነገሮችንም በአንክሮ እንዲከታተሉላቸው እንጠይቃለን፡፡ ይህንን ለእርስዎ የምንጽፈውን ደብዳቤ ለተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽነር፣ ለተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ ለዓለምአቀፉ የስደተኞች ድርጅት፣ ለአውሮፓ የስደተኞች ኮሚሽን፣ ለሰብዓዊ መብት ጥበቃ መ/ቤትና ለሌሎች የስደተኛ ጉዳይ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች በግልባጭ እንዲደርሳቸው ያደረግንን መሆናችንን በዚሁ አጋጣሚ እንዲያውቁልን እንወዳለን፡፡

ከላይ እንደጠቀስነው ይህ የጋራ ንቅናቄያችን በኢትዮጵያ ውስጥ የማኅበራዊ እኩልነት እንዲሰፍንና የሰብዓዊ መብት እንዲጠበቅ የሚታገል ድርጅት ነው፡፡ አባላቱም በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ሲሆን በበርካታ የዓለም ክፍሎች ቅርንጫፍ ቢሮዎች ከፍቶ የሚንቀሳቀስ ሕጋዊ ድርጅትም ነው፡፡

እርስዎ በውል ላይገነዘቡት ይችላሉ እንጂ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ በሥልጣን ላይ የሚገኘው አገዛዝ የሰብዓዊ መብት የሚጥስ፣ ሕዝቡን በከፋ ጭቆና የሚረግጥ ከመሆን አልፎ በተለያዩ ቦታዎች የዘር ማጥፋትን ወንጀል የፈጸመም ነው፡፡ ይህንን ዓይነቱን አገዛዝ የሚቃወሙ በርካታዎች ታስረዋል፣ ተገድለዋል፣ የደረሱበት ጠፍቷል፣ በሕይወት ያመለጡትም አገራቸውን ጥለው ለመሰደድ በቅተዋል፡፡ በተለይም በሊቢያ፣ በግብጽ እና በቱኒሲያ የለውጥ አብዮት በተካሄደበት ወቅት መግቢያ አጥተው ከነበሩት በመቶ ሺዎች ከሚቆጠሩት ስደተኛ ሠራተኞች መካከል ኢትዮጵያውያኖች ዋንኞቹ ነበሩ፡፡ ከእነዚህም መካከልም የተወሰኑት ወደማልታ ቢሄዱም እዚያ እንደደረሱ በማልታ ባለሥልጣናት ተይዘው ለእስር ተዳርገዋል፡፡

የጋራ ንቅናቄያችን ባለው መረጃ መሠረት ወደ ማልታ ከገቡት የምስራቅ አፍሪካ ስደተኞች መካከል የኤርትራና የሶማሊያ ዜጎች የተባበሩት መንግሥታት ባወጣው መመሪያ መሠረት ጥገኝነት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ኢትዮጵያውያኑ ግን ምንም እንኳን በአገራቸው ከፍተኛ የመብት ረገጣ የሰፈነ መሆኑ ቢታወቅም እስካሁን የጥገኝነት መብታቸውን ተነፍገው በእስር ይገኛሉ፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ በዘር ላይ የተመሠረተ ከፋፋይና ወገናዊ የሆነ አገዛዝ በመስፈኑ እነዚህ ኢትዮጵያውያን አገራቸው መኖር አልቻሉም፤ ውጪ ወጥተውም እንደዚህ ባለ ሰቆቃ ውስጥ ገብተው ይሰቃያሉ፡፡ ወደ አገራቸው ቢመለሱ አሁን ካሉበት ሁኔታ በባሰ ስቃይና እንግልት እንደሚገጥማቸው ስለሚያውቁ ኑሯቸውን በዚሁ ለመቀጠል መወሰናቸው አማራጭ ከማጣት መሆኑን ሊገነዘብላቸው የቻለ አካል አለመኖሩ እጅግ አሳዝኖናል፡፡ በተለይም በኦሮሚያና በኦጋዴን ክልሎች መጠነኛ የሆነ እርስበርስ ጦርነት እየተካሄደ በመሆኑ ከዚያ አካባቢ የሚመጡ በተለየ ሁኔታ ጥቃት የተጋለጡ ናቸው፡፡ በዓለም ዙሪያ የኢትዮጵያውያን ለስደትና ለሰቆቃ መጋለጣቸው የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡
እንደ (http://www.prosperity.com) ያሉት ድረገጾች ደግሞ ነጻነትን በተመለከተ ከዓለም አገራት ኢትዮጵያ ውራ እንደሆነች እየዘገቡ አገራቸው መኖር እያቃታቸው ለስደት ለተጋለጡ ኢትዮጵያውያን ተገቢውን ድጋፍ አለማግኘታቸው ለምን ይሆን ብለን እንድንጠይቅ ያስገድደናል፡፡

**ከየካቲት 2003ዓም ጀምሮ የጋራ ንቅናቄያችን በማልታ ስለሚገኙት ኢትዮጵያውያን መረጃ ሲቀበልና ከባለሥልጣናቱም ጋር ግንኙነት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡** በውጤቱም የተወሰኑት የስደተኛ መብታቸው የተከበረ ሲሆን ሌሎችም ወደ ሦስተኛ አገር ለመሄድ በቅተዋል፡፡ የአብዛኞዎቹ ጉዳይ ግን በእንጥልጥል መቆየቱና ለመኖርና ለጤናቸው እጅግ አስከፊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እስካሁን በእስር መቆየታቸው በጣም አሳስቦናል፡፡ **ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክነው መረጃ በግልጽ እንደሚያስረዳው 50 ኢትዮጵያውያን የታሰሩበትን ህንጻ፣ የእስረኛ ቁጥራቸውን፣ የአንዳንዶቹን ወቅታዊ ሁኔታ የሚገልጽ ዝርዝር ያካተተ ነው፡፡** አብዛኞዎቹ የህክምና ዕርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ከሐኪሞች የተወሰነ ቢሆንም በእስርቤት ኃላፊዎች እንቢተኝነት የዓለምአቀፉን ሕግ በሚጻረር መልኩ መብታቸው ተነፍጎ ይገኛል፡፡

ለምሳሌ ያህል **ሳሚራ አብዱ አህመድ (የእስረኛ ቁጥር 11C090)** የሚጥል በሽታ ያለባት በመሆኑ ሐኪሞች በተደጋጋሚ ክትትል እንደሚያስፈልጋት ቢያሳስቡም ይህ ባለመደረጉ ሕመሙ ጸንቶባት **ሕዳር 19፣2003 ዓም በ ማትር ዴ ሆስፒታል ሁለተኛ ፎቅ ላይ በኔኦሮ የህክምና ክፍል ተወስዳ ነበር፡፡** ከአራት ቀናት በኋላ ህዳር 24፣ 2003 **ሐኪሞች ‹‹ወደ እስር ቤት ከተመለሰች ግን ህመሟ የከፋ ደረጃ ይደርሳል›› የሚል ሙያዊ አስተያየታቸውን ቢሰጡም የእስር ቤት ኃላፊዎች ወደ እስር ቤት መልሰዋታል፡፡** ይህች ሴት ወደ ማልታ ከመምጣቷ በፊት በሊቢያ በነበረችበት ጊዜ ጤነኛና ጠንካራ ሠራተኛ የነበረች፣ ባለቤቷም በሌላ የስደተኛ እስርቤት የሚገኝ ሲሆን እርሱም ቢፈታ የባለቤቱን የህክምና ጉዳይ ለመከታተል የሚችል ነው፡፡ ሆኖም ኃላፊዎች ሁሉንም ጉዳይ በመቃወማቸው እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ትገኛለች፡፡

**በዚሁ ዓመት እስካሁን ሦስት ሰዎች የሞቱ በመሆናቸው ሰሚራ አራተኛዋ እንድትሆን ፈጽሞ አንሻም፡፡ ሆኖም ግን ይህ ጥሪያችን ሰሚ አጥቶ ሰሚራ ላይም ሆነ ሌሎች እስረኞች በሕወታቸው ላይ አንዳች ጉዳት ቢደርስ በዓለምአቀፍ ደረጃ ምርመራ ተደርጎ ወንጀሉን የፈጸሙ ተገቢውን የፍትሕ ብያኔ እንዲያገኙ እስከምናደርግ ድረስ የማናርፍ መሆናችንን እንገልጽልዎታለን፡፡**

ክቡር ሆይ፣

በማልታ የሚገኙት ኢትዮጵያውያን ጉዳይ እጅግ ከፍተኛ በሆነ መልኩ የምንከታተለው መሆኑን እየገለጽን ከእርስዎ መንግሥትና መስሪያቤት ጋር በትብብር ለመስራት ያለንን ዝግጁነት ለመግለጽ እንወዳለን፡፡ **አስፈላጊም ከሆነ የጋራ ንቅናቄያችን ማልታ ድረስ ልዑካን በመላክ ሁኔታው በአካል ተገኝቶ ለመከታተልና የእስረኞቹንም ሁኔታ በቅርብ ተከታትሎ እስከ ማስፈታት ያለውን ጽኑ ዝግጁነት ልናሳውቅዎ እንወዳለን፡፡**

በአሁኑ ወቅት ከሃምሳ በላይ ኢትዮጵያውያን ከዘጠኝ ወር በላይ ታስረው ይገኛሉ፡፡ **ይህ የዓለምአቀፉን ሕግ የሚጻረር ሕገወጥ ተግባር መቆም አለበት፤ እስረኞቹም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ባስቸኳይ መፈታት አለባቸው፡፡ ወደ ሦስተኛ አገር የሚሄዱትም ሆነ እዚያው የጥገኝነት ፈቃድ ሊሰጣቸው የሚገባቸው በሙሉ ባስቸኳይ ይህ መብታቸው እንዲከበር የእስርቤቶቹን ኃላፊዎች እናሳስባለን፡፡ እነዚህ ሰዎች ወንጀለኞች አይደሉም፤ የማልታን ኅብረተሰብ አደጋ ላይ የሚጥሉም አይደሉም፡፡ ወንጀል ተብሎ ሊጠቀስባቸው የሚችል አንድ ነገር ቢኖር ጥገኝነት ለማግኘት መረጃ ሳይዙ ወደ ማልታ መግባታቸው ብቻ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖ ግን አሁን ያላቸው ከፍተኛ ስጋት በማልታ በእስር ላይ መቆየታቸው ብቻ ሳይሆን ጨካኝ ለሆነው የኢትዮጵያ አገዛዝ ተላልፈው ይሰጣሉ የሚል ነው፡፡ ይህ ፍርሃቻቸው ከእስርና ህክምና ከማጣት ጋር ተቀላቅሎ በምን ዓይነት ሰቆቃ ላይ እንደሚገኙ መገመት የሚያቅተው ማንም አይኖርም፡፡**

ስለሆነም እነዚህ እስረኞች በአስቸኳይ የሚፈቱበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ከእኛ በኩል ማድረግ የሚገባንን ለመፈጸም ያለንን ቁርጠኝነት እየገለጽን በጉዳዩ ላይ የእርስዎን አፋጣኝ ምላሽ እንጠብቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር



ኦባንግ ሜቶ
ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ
ዋና ዳይሬክተር፡፡

**አድራሻ፡**
910 17th St. NW, Suite 419
Washington, DC 20006 USA
Phone 202 725-1616
Email: Obang@solidaritymovement.org
Website: www.solidaritymovement.org

**ግልባጭ፤**

ሌ/ኮ ብራያን ጋት
የማልታ የወኅኒ ቤቶች አገልግሎቶች ኮማንደር

አቶ አሌክሳንደር ቶርቴል
የጥገኝነት ጠያቂዎች መ/ቤት (AWAS) ኃላፊ

አቶ ጆን ሆሳኤር
በማልታ የተ.መ. የስደተኞች ጉዳይ ተወካይ

አባ ፊሊጶስ
የስደተኞች ጉዳይ ኮሚሽን ዳይሬክተር

ወ/ሮ ጃነት ዙፌል
በጄኔቫ የተ.መ. ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን

አቶ አንቶኒዮ ጉቴሬስ
የተ.መ. የስደተኞች ጉዳይ ኮሚሽነር

አቶ ባን ኪ-ሙን
የተ.መ. ዋናጸሐፊ

ወ/ት ናቫንተም ፒላይ
የተ.መ. የሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር

አቶ ሚካኤል ሪበንቪክ
የአውሮጳ የስደተኞች ጉዳይ ዋና ዳይሬክተር

የስደተኞች ጉዳይ ዓለምአቀፍ ድርጅት
የስደተኞች መብት ዓለምአቀፍ ኢኒሺዬቲቭ
አምነስቲ ኢንተርናሽናል በማልታ
የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅት

<u>ግልባጭ የተደረገላቸው የዜና አገልግሎቶች</u>
ማልታቱደይ ጋዜጣ
የቢቢሲ ዋና አርታኢ - ዮሴፍ ዋሩንጉ
የዋል ስትሪት ጆርናል ዋና አርታኢ - አለን መረይ
የኒውዮርክ ታይምስ ዋና አርታኢ
የዋሽንግተን ፖስት የውጪ ቢሮ
የጋርዲያን የዜና ዴስክና አርታኢ
የአልጃዚራ ዋና አርታኢ
የጋርዲያን - ማርቲን ሃሳን
የ ዘ ኢንዲፔንዳንት አርታኢ - ትሪስተን ዴቪስ
የ ዘ ታይምስ - ማርቲን ፍሌቸር
የዓለምአቀፉ የጋዜጦችና አሳታሚዎች ማኅበር ምክትል ዋና ኃላፊ ሌሪ ኪልማን

## <u>የታሳሪዎቹ ስም ዝርዝርና የታሰሩበት ሁኔታ ከነቁጥራቸው</u>

በአሁኑ ጊዜ በእስር ላይ የሚገኙትና መረጃዎቻቸውን ማግኘት የቻልነው ከዚህ በታች የሰፈረ ሲሆን ከእነዚህም የተወሰኑት የጋራ ንቅናቄያችን በታህሳስ ወር መጀመሪያ አካባቢ ለዓለምአቀፍ ድርጅቶች ጉዳያቸውን ባሳወቀው መሠረት ከእስር ቢለቀቁም በርካታዎቹ አሁን በእስር እየማቀቁ ይገኛሉ፡፡

## የታሰሩበት ቦታ፡ LYSTER BARRACKS፤ ZONE E AND ZONE C

| ተራ ቁ. | ስም | የእስረኛ ቁጥር | ያሉበት ሁኔታ |
|---|---|---|---|
| 1. | ቤኪ ኩማ ፋጂ | 11C220 | ከሊቢያ ልጇን ጥላ ወደዚህ የተላከች፣ በዚህም የተነሳ ለጭንቀት የተዳረገች፣ October 10 2011 ከ፯ ወር አስር በሁዋላ በ detention ኦፊሰሮች አማካይነት በገባላቸው መጠጥ የሰከሩ ፭ የናይጀርያ ዜግነት ያላቸው አስረኞች በፈላ ዘይት እና በጋለ ብረትድስት ጉዳት አድርሰዉባታል:: ሌሎች ፭ አትዮጵያዉያንንም ጎድተዋል:: |
| 2. | አሚና ሸሪፍ ሐቢብ | 11C 269 | |
| 3. | ጸሐይ ኦላና ዳባ | 11C264 | በእስር ምክንያት ሕመምተኛ የሆነች |
| 4. | ቅድስት ለሜሳ ኩማ | 11C275 | ለአቅመ ሔዋን ያልደረሰች እንዲሁም የአጥንት በሽታ ሕመምተኛ ስትሆን ምርመራ የተነፈጋት ነች፡፡ከሊቢያ ጦርነት ሸሽታ ማምለጧ ወንጀል የሆነባት፡፡ |
| 5. | አስቴር ይማም ተሰማ | 11C262 | |
| 6. | ጀሚላ ዑስማን ኑር | 11C278 | |
| 7. | ሊዲ ቢያ ሺፉ | 11f024 | በከፍተኛ የደም ግፊት አየተሰቃየች ያለች ህመሙ የጀመራት ከታሰረች በኋላ ባህር ላይ አስር ቀን ቆይታ በመሆኑ ለጥቂት በህይወት የተረፈች፤ |
| 8. | ታደለች አባተ ጩምባለ | 11C279 | |
| 9. | ሮማን ሞሐመድ አባሲመል | 11C272 | |
| 10. | ብርቱካን አብደላ አህመድ | 11C282 | በህመም አየተሰቃየች ያለች፣ ባለቤቷ ከጣልያን መጥቶ እንዲፈቱለት እንዲያሳክማት ቢማጸንም ሰሚ አጥቶ ተመልሷል፤ ያቀረበችው አቤቱታ ተቀባይነት በማጣቱ ለረጅም ጊዜ ታስራ እንደምትቆይ የተነገራት፤ |
| 11. | ሰሚራ ሞሐመድ አህመድ | 11a308 | በተደጋጋሚ ሀኪም አንድትፈታ ቢያሳስብም ከMarch 28/2011 ጀምሮ ታስራ አየተሰቃየች ትገኛለች። ያቀረበችው አቤቱታ ተቀባይነት በማጣቱ ለረጅም ጊዜ ታስራ እንደምትቆይ የተነገራት፤ |
| 12. | ፌቨን በፍቃዱ | 11C273 | March 29/2011 ከታሰረች በሁዋላ በሽተኛ ሆና ለሁለት ወራት በሆስፒታል ሕክምና ስትከታተል ቆይታ ህመሟ ከመታሰሯ ጋር የተያያዘ ጭንቀት በመሆኑ ትፈታ ብሎ ሀኪም በማዘዙ 22/12/2011 ብትፈታም አሁንም አግሯ ሙሉ ለሙሉ አይንቀሳቀስላትም ከህመምዋም ገና አላገገመችም። |
| 13. | ሕይወት ዓመዴ ተስማማ | 11C235 | በከፍተኛ ሕመምና የጭንቀት በሽታዎች ለ9 ወራት በመሰቃየት ላይ የምትገኝ። ሀኪም የበሽታዋን ከባድነት ገልፆ አንድትፈታ ቢያዝም ዛሬም እስር ላይ ትገኛለች። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 14. | ወገኔ ከተማ ለገሠ | 11C234 | |
| 15. | ቸርነት ጣሰው | 11C267 | |
| 16. | ወርቅነሽ ጎንፋ | 11C268 | |
| 17. | ከዲጃ ዱራ | 11a289 | |
| 18. | ሚኪያስ ጌታቸው | 11C089 | |
| 19. | ሰሚራ አብዱ | 11C090 | እዚያው እስር ቤታ ባጋጠማት የተለያዩ በሽታዎች ምክንያት የምትሰቃይና ሐኪሞች እንድትፈታ ቢጠይቁም የማልታ መንግስት ፈቃደኛ ባለመሆን መስኮቱ በተሰባበረ እስር ቤት ያለ ወንጀሏ እየተሰቃየች የምትገኝ፤ |
| 20. | ሐቢብ ዘማቹ | 11C199 | |
| 21. | ተስፋዬ ይርጉ | 11d012 | ከታሰረ በኋላ የደም ግፊት ይዞት እየተሰቃየ የሚገኝ፤ |
| 22. | ወዛም ኃይለማሪያም | 11d013 | |

## የታሰሩበት ቦታ፡ SAFI BARRACKS WAREHOUSE 1

| | | | |
|---|---|---|---|
| 23. | መርከብ ኃይሉ ዲያና | 11C186 | |
| 24. | ያሬድ ደሳለኝ ተክለማሪያም | 11C171 | ከታሰረ በሁዋላ ለአእምሮ ህመም ተዳርጎ የሚሰቃይ |
| 25. | ይታገሱ ለገሠ ተክለማሪያም | 11C187 የትውልድ ዘመን (03/23/1994) | የአጥንት ምርምራ እንኳን እንዲደረግለት ቢጠየቁ አሻፈረኝ በማለት ካለዕድሜው በእስር የሚሰቃይ፤ |
| 26. | ብስራት ገመቹ አብደቿሳ | 11C 107 | |
| 27. | ምጽባህ ኑር ሞሐመድ | 11C138 | |
| 28. | ሞሐመድ ኑር አህመድ | 11C 173 | |
| 29. | ገበየሁ ጥሩነህ ገብረሕይወት | 11b 134 | |
| 30. | ጋሻው ዱላ አበራ | 11C188 | |
| 31. | ዮናስ ተኮላ አበበ | 11C185 | |
| 32. | ጥላሁን ይማም ሞሐመድ | 11C238 | |
| 33. | አምላክባለው በየነ አባተ | 11a322 | |
| 34. | ሃይማኖት (የአእምሮ በሽተኛ) | | የአእምሮ ህመምተኛ ሆኖ ሕክምና እንኳን አግኝቶ የማያዉቅ ስሙን ወይም ዜግነቱን እንኳን የማያስታውስ |

## የታሰሩበት ቦታ፡ SAFI BARRACKS BLOCK B

| | | | |
|---|---|---|---|
| 35. | ግርማ አበራ ነጋ | 11C164 | |
| 36. | ጸሐዬ ገብረሐዋሪያት ገብረሃናኒያ | 11C168 | |
| 37. | ፋሲል ሳምሶን ኃይለማሪያም | 11C108 | |
| 38. | ቢኒያም ተስፋዬ ሃብተጊዮርጊስ | 11C189 | |
| 39. | አብዱ ሳቢር ጁሐር | 11C140 | |
| 40. | ኢስማኤል ሲራጅ ኢብራሒም | 11C156 | |
| 41. | ቢኒያም አበበ ቸኮል | 11C035 | |
| 42. | ሙከሚል ኑሪ አወል | 11C059 | |
| 43. | ጀማል ሁሴን ሞሐመድ | 11C155 | |
| 44. | ዮናስ ተክሌ ሃይሌ | 11C170 | |
| 45. | ተመስገን ክፍሌ ኃይለማሪያም | 11e100 | |
| 46. | ዳንኤል ልደቴ ቃንቁሬ | 11e064 | የአካል ጉዳተኛ ቢሆንም የሃኪምን ትእዛዝ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ባለማክበር እስከ NOV. 2011 ድረስ የታሰረ |
| 47. | ቢራቱ ሚዘና | 11C146 | ለአንድ ወር ከሃያ ቀናት ሆስፒታል ተኝቶ ወደ እስርቤት የተመለሰ፤ በዕድሜ የገፋ ግለሰብ ሲሆን ለስምንት ወራት የታሰረ |
| 48. | አስፋው ሙገታ ለሴ | 11C157 | |
| 49. | ኑሩ ሞሓሚ አብቃድር | 06C007 | |
| 50. | ቶፊቅ በርታ ሸሪፍ | 11b140 | |